መልእክት ስድስት

## ዘላለማዊው ንጉሥ ክርስቶስ
## ምድርን የራሱ ለማድረግ መምጣቱ
## እና
## የእግዚአብሔር ምሥጢር መፈጸም

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 10፥1-7፤ 11፥15-18

**I. ራእይ 11፥15-18 እና 12፥10 ክርስቶስን እንደ ዘላለማዊው ንጉሥ መለማመድ እና መደሰት እንደምንችል ያመለክታሉ፦**

ሀ. "የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል"—11፥15፦

1. ሰባተኛው መለከት ሲነፋ፣ የታላቁ መከራ ማብቃቱ ብቻ ሳይሆን ይህም ዘመን ይዘጋል፣ የእግዚአብሔርም ምሥጢር ይፈጸማል (10፥7)፣ ሌላ ዘመን፣ የመንግሥቱ ዘመን፣ የሺው ዓመት ይጀምራል።
2. ክርስቶስ በአሕዛብ ላይ ፍርዱን ከፈጸመ በኋላ ተመልሶ ሲመጣ የዓለም መንግሥት የእርሱ መንግሥት ትሆናለች—ዳን. 7፥13-14፤ 2፥44-45።
3. እዚህ ጋር የጌታ ለዘላለም እስከ ዘላለም መንገሥ የጌታ በሺው ዓመት መንግሥት እና በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር ለዘላለም መንገሥ ነው—ራእ. 22፥5።

ለ. "አቤቱ፥ አንተ ለዘላለም ትኖራለህ፤ ዙፋንህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ነው"—ሰቆ. 5፥19፦

1. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ማንነት እና ዙፋኑ ከምሕረቱ፣ ከርኅራኄው እና ከታማኝነቱ በላይ ከፍ ያሉ ናቸው—3፥22-23።
2. የእግዚአብሔር ምሕረት እና ርኅራኄ ሊለዋወጡ ይችላሉ፣ የእግዚአብሔር ማንነት እና አገዛዙ ግን ለዘላለም ሳይለዋወጡ ይኖራሉ።
3. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ እግዚአብሔር እንደ ዘላለማዊው ንጉሥ በማንነቱ እና እንደ ዘላለማዊው፣ የማይናወጥ መንግሥቱ በአገዛዙ ሙሉ በሙሉ ይገለጣል (ዕብ. 12፥28፤ ራእ. 22፥3)፤ ማንነቱና አገዛዙ፣ ሁለቱም ከሕዝቡ ጋር ላለው ግንኙነት የማይናወጥ መሠረት ናቸው።

**II. በራእይ 10፥1-7 ምድርን የራሱ ሊያደርግ የሚመጣው ክርስቶስ የጠራ ራእይ አለን፦**

ሀ. በዚህ ምዕራፍ፣ በ7፥2፤ 8፥3 እና 18፥1 እንዳለው ክርስቶስ "ሌላ ብርቱ መልአክ" ነው።

ለ. ዮሐንስ ሌላ መልአክ "ከሰማይ ሲወርድ" አየ—10፥1፦

1. ክርስቶስ አሁን ከሰማይ እየወረደ ነው።
2. ይህ ራእይ ክርስቶስ ወደ ምድር አሁንም በመምጣት ላይ እንዳለ ፍንጭ ነው።

ሐ. ክርስቶስ "ደመና ተጎናጽፎአል"—ቁ. 1፦

1. በ14፥14 እና በማቴዎስ 24፥30፤ 26፡64 ላይ እንዳለው ገና "በደመና ላይ" አይደለም።
2. "በደመና ላይ" መሆን በገሃድ መምጣት ነው፣ "ደመና ተጎናጽፎ" ደግሞ በስውር መምጣት ነው።
3. በራዕይ 1፥7 እና በማቴዎስ 24፥30 ላይ እንደተጠቀሰው ክርስቶስ በምድር ወገኖች ሁሉ እስኪታይ ድረስ በገሃድ ሳይሆን በስውር ይመጣል።
4. በራእይ 10 ጊዜ እንኳን፣ የክርስቶስ መምጣት አሁንም ምሥጢር ነው።
5. በደመና ላይ ተቀምጦ መምጣቱ በገሃድ እስከሚሆንበት እስከ ምዕራፍ 14 ድረስ በደመና ይሸፈናል።
6. በዚህም ከታላቁ መከራ በፊት ክርስቶስ እንደሚመጣ የሚናገረው የተለመደ ትምህርት የተሳሳተ መሆኑን ማየት እንችላለን።

መ. "በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ"—10፥1፦

1. እዚህ ጋር ቀስተ ደመናው፣ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲፈርድ እና ምድርን የራሱ ለማድረግ ሲመጣ ምድርን በተመለከተ እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚጠብቅ ያመለክታል—ዘፍ. 9፥8-17።
2. በተጨማሪም ክርስቶስ በዙሪያው ቀስተ ደመና ባለው ዙፋን ላይ በሚቀመጠው በእግዚአብሔር መሠረት ፍርድን የሚፈጽመው መሆኑንም ያመለክታል—ራእ. 4፥2-3።
3. የራእይ መጽሐፍ እግዚአብሔር ምድርን እና በእርሷ ውስጥ በሚኖሩ ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ ይገልጣል።

4. በዙፋኑ ዙሪያ ያለው ቀስተ ደመና፣ እግዚአብሔር በምድር ላይ ፍርዱን እየፈጸመ ሳለ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ፣ የቃል ኪዳን አምላክ፣ ታማኙ አምላክ እንደሆነ ያመለክታል።
5. ዳግም በሰው ልጆች ላይ በጥፋት ውኃ አይፈርድም፣ የሰው ልጆችንም ሁሉ አያጠፋም፣ ነገር ግን ለክብሩ የአዲሱ ምድር አሕዛብ እንዲሆኑ ከሰው ልጆች ውስጥ የተወሰነውን ክፍል ጠብቆ ያቆያል—21፥24፣ 26።

ሠ. "ፊቱም እንደ ፀሐይ እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች ነበሩ"—10፥1፡-
1. በምድር ላይ ወዳሉ ሰዎች በገሃድ በሚመጣበት ጊዜ አቅራቢያ፣ ክርስቶስ ከጨለማው ጊዜ በፊት፣ ጎህ ከመቅደዱ በፊት እርሱን ለሚወዱት እና እርሱን ለሚጠባበቁት እንደሚገለጠው እንደ ንጋት ኮከብ ሳይሆን እንደ ፀሐይ ይሆናል።
2. በቁጥር 1 ላይ እሳት የሚያመለክተው ክርስቶስ በምድር ላይ ፍርዱን የሚፈጽምበትን የእግዚአብሔርን ቅድስና ነው (ዘጸ. 19፥18፤ ዕብ. 12፥29)።

ረ. "ቀኝ እግሩንም በባሕር ላይ ግራውንም በምድር ላይ አኖረ"—ራእ. 10፥2፡-
1. ክርስቶስ እግሮቹን በባሕር ላይ እና በምድር ላይ ማድረጉ በእነርሱ ላይ መረማመዱ ነው፣ በእነርሱ ላይ መረማመድ ደግሞ እነርሱን የራሱ ማድረግ ነው—ዘዳ. 11፥24፤ ኢያሱ 1፥3፤ መዝ. 8፥6-8።
2. ይህ የሚያመለክተው ክርስቶስ ምድርን የራሱ ለማድረግ እየመጣ እንደሆነ ነው።
3. የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ መጽሐፍ ለመክፈት የተገባው እርሱ ብቻ ነው፣ ምድርን የራሱ ለማድረግ ብቁ የሆነውም እርሱ ብቻ ነው።

ሰ. "እንደሚያገሣም አንበሳ በታላቅ ድምፅ ጮኸ"—ራእ. 10፥3፡-
1. የአንበሳ ግሣት በንጉሥ ቁጣ ተመስሏል—ምሳ. 19፥12፤ 20፥2።
2. ይህ የሚያመለክተው እንደ የምድር ንጉሥ ክርስቶስ በከፍተኛ ቁጣ እስኪቆጣ ደረሰ እንዳስቆጡት ነው።

## III. "የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል"—ራእይ 10፥7፡-

ሀ. ከአዳም እስከ ሙሴ እና ከሙሴ እስከ ክርስቶስ ባሉት መግቦተ ዘመናት፣ ሁሉም ነገር ተገልጦ ነበር፣ ምሥጢርም አልነበረም።

ለ. በሺው ዓመት መንግሥት መግቦተ ዘመን እና በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር፣ ሁሉም ነገር ይገለጣል፣ ምሥጢርም አይኖርም።

ሐ. ከክርስቶስ እስከ ሺው ዓመት መንግሥት ባለው መግቦተ ዘመን—በቤተ ክርስቲያን ዘመን፣ በጸጋ ዘመን—ሁሉም ነገር ምሥጢር ነው፡-
1. የክርስቶስ ተሠግዎ፣ እንደ የምሥጢር መግቦተ ዘመን መጀመሪያ፣ ምሥጢር ነው—1 ጢሞ. 3፥16፡-
   ሀ. በክርስቶስ ተሠግዎ፣ ወሰን የሌለው አምላክ ውስን ወደሆነው ሰው ውስጥ መጣ።
   ለ. እግዚአብሔር ወልድ ብቻ ሳይሆን መላው አምላክ ሥጋ ለበሰ፤ ስለዚህም፣ ክርስቶስ በተሠግዎ የመላው እግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ ነው።
2. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው—ቆላ. 2፥2፡-
   ሀ. እግዚአብሔር ምሥጢር ነው፣ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ለመግለጥ እንደ የእግዚአብሔር አካል መልበስ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው።
   ለ. እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አካል መልበስ፣ የእግዚአብሔር ፍቺ እና መብራራት ነው፤ እግዚአብሔር ለማድረግ የወጠነው ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የተያያዘ ነው።
   ሐ. በክርስቶስ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራል፤ ማለትም፣ የሦስታንዱ አምላክ ሙላት በክርስቶስ ውስጥ በሰው ተክለ-ሰውነት መልክ ይኖራል ማለት ነው—ቁ. 9።
3. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ምሥጢር ናት—ኤፌ. 3፥4-6፡-
   ሀ. ክርስቶስ ምሥጢር ነው፣ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ክርስቶስ አካል እርሱን ለመግለጥ የክርስቶስ ምሥጢር ናት።
   ለ. ይህ ምሥጢር፣ እግዚአብሔር ብዙዎች የተካተቱበትን መገለጥ ያገኘ ዘንድ፣ በክርስቶስ የእግዚአብሔር አካል መልበስ መጨመር እንዲሆን አካልን ለማፍራት፣ የእግዚአብሔር አካል መልበስ የሆነውን ክርስቶስን በእግዚአብሔር ወደ ተመረጡት ሕዝብ ውስጥ ማደል የሆነው የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ነው።
   ሐ. ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን እንደ አንድ መንፈስ ታላቁ ምሥጢር ናቸው—5፥32።

4. መንግሥተ ሰማያት (ማቴ. 13፥11)፣ ወንጌል (ኤፌ. 6፥19)፣ በውስጥ የሚኖረው ክርስቶስ (ቆላ. 1፥27) እና እንደ የምሥጢር ዘመን ፍጻሜ የሚመጣው የቅዱሳን ትንሣኤና በክብር መለወጥ (1 ቆሮ. 15፥51-52) ሁሉም ምሥጢራት ናቸው።
5. ሰባተኛው መለከት ሲነፋ፣ እነዚህ ሁሉ ምሥጢራት ይጠናቀቃሉ፤ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል።

© 2025 Living Stream Ministry